# አገልግሎትን ከእግዚአብሔር መቀበልና መፈጸም

*እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ (ዮሐንስ 17፡4)*

አሁን ባለንበት ዘመን ስለ አገልግሎት በአትኩሮት ማሰብ በአገልጋዮችና በምዕመናን ዘንድ ቸል የተባለበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አሳሳቢ እየሆነ የመጣበት ጊዜ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ስለ አገልግሎት በጉባኤ ማስተማር ብዙ የተለመደ አይደለም፡፡ ስለ አገልግሎት ትምህርት የምንሰጠው በዘርፍ አገልጋዮች ፕሮግራም ላይ ወይም የተለያዩ የአገልግት ቡድኖች ፕሮግራም ሲያዘጋጁ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ የተነሳ በሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን (አባላት) ያሉአቸው አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀሩ የአገልጋዮች እጥረት እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ምናልባት ምዕመናንን ስለ አገልግሎት ባለማስተማራችንና ለአገልግሎት እንዲነሳሱ ባለማድረጋችን ሊሆን ይችላል፡፡

ነገር ግን አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳችን ከመጀመርያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ አጽንዖት የሚሰጠውና ምዕመናንን በሙሉ የሚመለከት አንዱ ጉዳይ ነው፡፡ የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች የማይሳተፉበት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እስከ መቼውም ቢሆን ፍሬያማ ሊሆን አይችልም፡፡ የአማኞችን የክህነት አገልግሎት (ካህንነት) የዘነጋ ከመሆኑ የተነሳ መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለም፡፡ ስለዚህ አገልጋዮችን ለመተካትና ብዙ አማኞች (ጸጋና ኃይል የተላበሱ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ወጣቶችን ጨምሮ) ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማነሳሳት ስለ አገልግሎት ማስተማር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ምዕመናን በሚሳተፉበት በእንዲህ ዓይነት ጉባኤ ላይ ስለ አገልግሎት ትምህርት ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡

## 1. <u>አገልግሎት ምንድን ነው?</u>

አገልግሎት ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ 1ኛ ቆሮንቶስ 12 ጥሩ መልስ ይሰጠናል፡፡ ጳውሎስ ይህንን ምዕራፍ *"ስለ መንፈሳዊ ነገርም÷ ወንድሞች ሆይ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ" (ቁ. 1)* በማለት ይጀምራል፡፡ ይህ በቁጥር 1 የሚገኘው <u>*መንፈሳዊ ነገር*</u> የሚለው ሀረግ በሌሎቹ የምዕራፉ ክፍሎች ውስጥ በግልጽ <u>*"የጸጋ ስጦታ/መንፈሳዊ ስጦታ"*</u> ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ (<u>ምሳሌ፦</u> "<u>*የፀጋ ስጦታ"*</u> - ቁ. 4) ፡፡

> *<u>**የጸጋም ስጦታ**</u> ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ <u>**አገልግሎትም**</u> ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ <u>**አሠራርም**</u> ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ <u>ለእያንዳንዱ</u> ለጥቅም ይሰጠዋል፡፡ (1 ቆሮንቶስ 12፡4-7)*

**የጸጋ ስጦታ - አገልግሎት - አሰራር** የሚሉት ሃሳቦች በመመካከላቸው እጅግ በጣም ቅርርብና ግንኙነት እንዳላቸው ክፍሉ ያሳየናል፡፡ የጸጋ ስጦታዎች እጅግ ብዙ እንደመሆናቸው (ከ25 በላይ) አገልገሎትም እጅግ ብዙ ዓይነት ነው፡፡ በተጨማሪ አገልግሎት ልዩ ልዩ እንደመሆኑ

አሰራሩም ልዩ ልዩ ነው። ይሁን እንጂ የጸጋ ስጦታን የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው፤ የምናገለግለው ጌታ አንድ ነው፤ በእኛ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር አንድ ነው።

**ስለዚህ አገልግሎት በዚህ ዓለም ስንኖር መንፈስ ቅዱስ በሰጠን ማንኛውም የጸጋ ስጦታ (መንፈሳዊ ስጦታ - መለኮታዊ ችሎታ - ልዕለ ተፈጥሮአዊ ችሎታ) ከሐዋርያቱ የጸሎትና የቃሉ አገልግሎት ጀምሮ (ሐዋርያት ሥራ 6:4) እስከ ማዕድ አገልግሎት ድረስ (ሐዋርያት ሥራ 6:2) ያለውን መንፈሳዊ ስራ በእግዚአብሔር ድንቅ አሰራር በእግዚአብሔር እርሻ ወይም በእግዚአብሔር ሕንጻ ውስጥ መስራት ነው።**

እንግዲያው አገልግሎት የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስፋት ሲባል መንፈስ ቅዱስ በሰጠን መንፈሳዊ ስጦታ አማካይነት በእግዚአብሔር ቤት የምናከናውነው ማኛውንም ሥራ ወይም ተግባር የሚያካትት ነው። ይህ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቦታ (ሕንጻ)፣ በቅዱሳን ቤትና በሌሎች ቦታዎችም ጭምር የሚከናወኑትን አገልግሎቶች ይጨምራል።

## 2. አገልጋይ ማን ነው?

"አገልጋይ ማን ነው?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ "የጸጋ ስጦታ የተሰጠው ለማን ነው?" የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ይሆናል። የጸጋ ስጦታ የተሰጠው ለአማኞች በሙሉ ነው።

> *<u>የጸጋም ስጦታ</u> ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ <u>አገልግሎትም</u> ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ <u>አሠራርም</u> ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ <u>ለእያንዳንዱ</u> ለጥቅም ይሰጠዋል። (1 ቆሮንቶስ 12:4-7)*
>
> *ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ <u>እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ</u> መጠን <u>በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤</u>* (1 ጴጥሮስ 4:10)

ከላይ ከተመለከትናቸው ጥቅሶች እንደምንመለከተው መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ ስጦታ ወይም የጸጋ ስጦታ ሰጥቷል። እያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ አንድ የጸጋ ስጦታ አለው። እያንዳንዱ አማኝ የጸጋ ስጦታ ካለው እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ያዘጋጀው አገልግሎት አለ ማለት ነው።

ስለዚህ ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እነደምንመለከተው <u>ምንም እንኳ የአገልግሎት ጥሪ ዓይነት፣ የአገልግሎታችን የስፋት መጠን፣ የአገልግሎት ጊዜና የአገልግሎት ስፍራ የተለያየ ቢሆንም አማኞች በሙሉ አገልጋዮች ናቸው።</u> ጴጥሮስ ስለ ክርስቲያኖች የክህነት አገልግሎት የተናገረው አማኞች በሙሉ አገልጋዮች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው። <u>በአዲስ ኪዳን ሁሉም አማኞች አገልጋዮች ናቸው።</u>

*<u>እናንተ</u> ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን <u>የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ</u> የተመረጠ ትውልድ፥ <u>የንጉሥ ካህናት፥</u> ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤* (1 ጴጥሮስ 2፡9)

ስለዚህ ምንም እንኳ የጸጋ ስጦታዎቻቸውን ባለመለየት/ባለማወቅ፣ ወይም ደግሞ ጸጋቸውን ለይተው አውቀው ነገር ግን ጊዜ ለመስጠትና መስዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኝነት ባለመኖር፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት፣ ወዘተ ወደ አገልግሎት ያልገቡ አማኞች ቢኖሩም <u>እንደ እግዚአብሔር ቃል ስንመለከተው በመለኮታዊ መርህ አማኞች በሙሉ አገልጋዮች ናቸው።</u>

በዚህ አጋጣሚ ወደ አገልግሎት ያልገቡ አገልጋዮች ጸጋቸውን በመለየትና ለእግዚአብሔር ስራ ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኞች በመሆን በዚህ ዓመት አገልግሎት እንዲጀምሩና እግዚአብሔር በሕይወታቸው ሊሰራ ያቀደውን ድንቅ ስራ እንዲያስተናግዱ አነሳሳለሁ። በተጨማሪ ይህ ትምህርት አማኞችን ሁሉ የሚመለከት ስለሆነ ሁላችሁም የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ለሆነው የእግዚአብሔር ቃል ልባችሁን እንድትከፍቱ በጌታ ስም አሳስባለሁ።

## 3. <u>አገልግሎት ከጥሪ ይጀምራል</u>

### 3.1 <u>የድነት ጥሪ</u>

*እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ <u>ወደ እኔ ኑ</u>፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። (ማቴዎስ 11፡28)*

*በገሊላ ባሕርም አጠገብ ሲያልፍ ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። እርሱም (ኢየሱስ)፦ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው። ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት። (ማርቆስ 1፡16-18)*

*ከዚያም ጥቂት እልፍ ብሎ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ደግሞ በታንኳ ላይ መረባቸውን ሲያበጁ አየ። ወዲያውም ጠራቸው አባታቸውንም ዘብዴዎስን ከሞያተኞቹ ጋር በታንኳ ላይ ትተው ተከትለውት ሄዱ። (ማርቆስ 1፡19-20)*

በአጭሩ አገልግሎት ክርስቶስን ከመከተል ይጀምራል። ክርስቶስን በአግባቡ ሳይከተሉ አገልግሎትን መሞከር ሞያተኛ እንጂ የእግዚአብሔር መልእክተኛ አያደርገንም።

*የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል። (ዮሐንስ 12፡26)*

### 3.2 <u>የአገልግሎት ጥሪ</u>

*እንግዲህ <u>ሂዱና</u> አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት <u>አድርጓቸው</u>፤ ... (ማቴዎስ 28፡19-20)*

አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው። ... እነዚህን አሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፥ ... (ማቴዎስ 10፡1፣5)

*ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ <u>ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና</u> (ሐዋርያት 9፡15)*

*ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም፤ ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበት ነገር <u>አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና።</u> (ሐዋርያት 26፡16)*

## 4. <u>አገልግሎት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ነው</u>

*እኔ ላደርገው <u>የሰጠኸኝን ሥራ</u> ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ (ዮሐንስ 17፡4)*

*ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን <u>የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥</u> ከእግዚአብሔር ነው፤ (2 ቆሮንቶስ 5፡18)*

ከእግዚአብሔር የተቀበልነው አገልግሎት ሁለት ነገሮችን አብሮ ያካተተ ነው። እነዚህም፡-

**ሀ) <u>ኃላፊነት</u>**

ዮሐንስ 21፡15-17 - ግልገሎቼን አሰማራ፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ፣ በጎቼን አሰማራ፤
ማቴዎስ 28፡20 - ደቀመዛሙርት አድርጓቸው

**ለ) <u>ተጠያቂነት</u>**

ሕዝቅኤል 3፡18-20 - ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ
1 ቆሮንቶስ 3፡12-15 - አገልግሎታችን በእሳት ይፈተናል
1 ቆሮንቶስ 9፡16 - ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ
ማቴዎስ 25፡14-30 - አንተ በጎ ታማኝ ባርያ (ቁ. 23)
- አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባርያ (ቁ. 26)

## 5. <u>አገልግሎት ግልጽ የሆነ ዓላማ አለው</u>

*አገልግሎት ግልጽ ዓላማ ያለው ነው።*

### 5.1 <u>አገልግሎት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ነው</u>

*እንዲህም አላቸው፦ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። <u>ያመነ</u> የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል። (ማርቆስ 16፡15-16)*

### 5.2 <u>አገልግሎት አማኞች ክርስቶስን እንዲመስሉ ለመርዳት ነው</u>

*ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ <u>የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥</u> (ኤፌሶን 4፡12)*

*እኛም <u>በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን</u> ሁሉ እናቀርብ ዘንድ (ቆላስይስ 1፡28) የአገልግሎት ዓላማ በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰው ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው።*

### 5.3 <u>አገልግሎት አማኞችን ለአገልግሎት ብቁ ለማድረግ ነው</u>

*<u>ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና</u> ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ። (ኤፌሶን 4፡13)*

## 6. <u>አገልግሎት መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን መንፈሳዊ ስጦታ የሚከናወን ነው</u>

### 6.1 <u>መንፈሳዊ ስጦታ ምንድን ነው? (1 ቆሮንቶስ 12፡4-10)</u>

መንፈሳዊ ስጦታ እያንዳንዱ ክርስቲያን በክርስቶስ አካል ውስጥ በቀላሉ ያለ ምንም ትግል፣ ችግርና ክብደት ውጤታማና ፍሬያማ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመስራትና ለማገልገል በእግዚአብሔር ጸጋ እንዲሁ በነጻ ከመንፈስ ቅዱስ የምንቀበለው ልዩ መለኮታዊ (ልዕለ ተፈጥሮዓዊ) ችሎታ ነው።

ይህ ስጦታ የሚሰጠው በጌታ ነው፣ በዓይነት መንፈሳዊ ነው፣ እንደዚሁም በትግል ሳይሆን በእግዚብሔር ቸርነት በቀላሉ ከመንፈስ ቅዱስ የምንቀበለው ነው። መንፈሳዊ ስጦታችንን በመጠቀም እርምጃ ስንወስድ አማኞች በሙሉ (ቤተ ክርስቲያን) ይጠቀማሉ። ይህ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ለሌሎች ክርስቲያኖች የምናደርገው እጅግ ታላቅ የሆነ እንደዚሁም በጣም ውጤታማና ፍሬያማ የሆነው አስተዋጽዖአችን ስጦታችንን መለማመድ (በተግባር መግለጥ) ነው።

### 6.2 <u>መንፈሳዊ ስጦታ ለምን ይሰጣል?</u>

ሀ) ለወንጌል ሥርጭት

ለ) ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ (1 ቆሮንቶስ 14፡12፤26)

## 7. <u>አገልግሎት የሚጀመር ብቻ ሳይሆን የሚፈጸም ነው</u>

<u>ኢየሱስ ክርስቶስ</u>

*ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ <u>**ሥራውንም እፈጽም**</u> ዘንድ ነው። (ዮሐንስ 4፡34)*

*እኔ <u>**ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ**</u> በምድር አከበርሁህ፤ (ዮሐንስ 17፡4)*

<u>ጳውሎስ</u>

*ሩጫውን <u>**ጨርሼአለሁ**</u>፥ (2 ጢሞቴዎስ 4፡7)*

<u>ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ</u>

*አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ <u>**አገልግሎትህን ፈጽም።**</u> (2 ጢሞቴዎስ 4፡5)*

<u>ጳውሎስ ለአክሪጳ</u>

*ለአክሪጳም። በጌታ <u>**የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽመው**</u> ተጠንቀቅ በሉልኝ። (ቆላስይስ 4፡17)*

## 8. <u>አገልግሎታችንን የመፈጸማችን መለኪያ ወደ አገልግሎት ዓላማ መድረሳችን ነው</u>

ሀ) ሰዎችን በወንጌል ስብከት ወደ ክርስቶስ መምጣታቸው

ለ) ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ትምህርት የተነሳ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ፍሬ በማፍራት ክርስቶስን ወደ መምሰል ማደጋቸው

ሐ) አማኞች መንፈሳዊ ስጦታቸውን እንዲለዩና እንዲለማመዱ በማድረግና በአገልግሎት እንዲያድጉ በመርዳታችን ለአገልግሎት ብቁ መሆናቸው

## 9. <u>አገልግሎታችንን በአግባቡ ፈጽመን የምናልፈው እንዴት ነው?</u>

### 9.1 <u>በአስተምህሮና በምንኖረው ሕይወት ሐይማኖትን በመጠበቅ</u>

አገልጋይ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱና በሕይወቱ መካከል ምንም ተቃርኖ ሊኖረው አይገባም። ይልቁንም ሕይወቱና ትምህርቱ መጣጣም ወይም አንድነት ሊኖረው ይገባል። የጳውሎስ ቃሉና ተግባሩ የተጣጣሙ ነበሩ። ለሌሎች የሚናገረው ሁሉ በራሱም ሕይወት የሚገለጥና እንዲሆን የሚፈልገው ነው።

<u>ጳውሎስ እውነተኛውን ከጌታ የተቀበለውን ትምህርት ጠበቀ።</u>

*ሃይማኖትን <u>**ጠብቄአለሁ፤**</u> (2 ጢሞቴዎስ 4፡7)*

<u>ጳውሎስ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ያለ ነቀፋ ኖረ፣ ተግባራዊ የክርስትና ሕይወት ኖረ።</u>

*ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና፤ <u>**በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደ ነበርን ታውቃላችሁ።**</u> (1 ተሰሎንቄ 1፡5)*

*በእናንተ በምታምኑ ዘንድ <u>በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን፥</u> እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ፤ (1 ተሰሎንቄ 2፡10)*

9.2 <u>በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመደገፍ</u>

አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚከናወን ነው?

<u>ኢየሱስ</u>

*ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ <u>የእግዚአብሔርም መንፈስ</u> እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፥ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። (ማቴዎስ 3፡16-17)*

<u>ደቀ መዛሙርት</u>

*ነገር ግን <u>መንፈስ ቅዱስ</u> በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ <u>ኃይልን ትቀበላላችሁ፥</u> በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ <u>ምስክሮቼ ትሆናላችሁ</u> አለ። (ሐዋርያት 1፡8)*

<u>ጳውሎስ</u>

*አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፥ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፥ <u>በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው</u> በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤ ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ፤ ሰብኬአለሁ። (ሮሜ 15፡18-19)*

*ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ <u>በኃይል እንደሚሠራ</u> እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ። (ቆላስይስ 1፡29)*

9.3 <u>ቃሉን ማዕከል ያደረገ አገልግሎት በማገልገል</u>

እውነተኛ አገልግሎት ዓላማውን የሚጨብጥበትን መንገድ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው። ይህም መንገድ ሰውን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በመገሰጽና በማስተማር ነው።

<u>ኢየሱስ ያገለገለው አባቱ የሰጠውን ቃል በማስተማር ነው፡-</u>

*<u>የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤</u> እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ። (ዮሐንስ 17፡8)*

*<u>ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው ተልዕኮ ያዘዛቸውን (ቃሉን) እንዲያስተምሩ ነው፡-</u>*

*<u>ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው</u> ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። (ማቴ 28፡20)*

<u>የጳውሎስ አገልግሎት ቃሉን ማዕከል ያደረገ ነበር፡-</u>

*ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ <u>እያስተማርን</u> (ቁ. 28ለ)*

*<u>የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንምና፤</u> በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደ ተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን። (2 ቆሮ 2፡17)*

9.4 <u>ክርስቶስን በመስበክ</u>

እውነተኛና ውጤታማ አገልግሎት የትምህርቱንና የስብከቱን ጭብጥ (መካከለኛ/ማዕከል) ኢየሱስ ክርስቶስን ያደረገ ነው።

*የምንሰብከው <u>እርሱ</u> (ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው። (ቆላስይስ 1፡28ሐ)*

*እኛ ግን <u>የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤</u> ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፥(1 ቆሮንቶስ 1፡23)*

*<u>ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና፥</u> ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን። (2 ጢሞቴዎስ 4፡5)*

9.5 <u>ለትጋትና ለተጋድሎ ራሳችንን በመስጠት</u>

*በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ <u>እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ።</u> (ቆላስይስ 1፡29)*

*መልካሙን ገድል <u>ተጋድዬአለሁ</u>፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ (2 ጢሞቴዎስ 4፡7)*

*ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን <u>ደከምሁ፥</u> ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም። (1 ቆሮንቶስ 15፡10)*

*ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ <u>ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።</u> (ሐዋርያት 20፡24)*

9.6 <u>በጸሎት ሁልጊዜ ራስን አሳልፎ ለእግዚአብሔር በመስጠት</u>

አገልግሎት መስቀል የሚበዛበት ስለሆነ ለራሳችንና ለሌሎች ልንጸልይ ይገባል።

<u>ኢየሱስ</u>

*እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም ልጅ*

*ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ ... ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው:: (ዕብራውያን 5፡7-8፣ 10)*

<u>ጳውሎስ</u>

በሐዋርያት ሥራና በመልዕክቶች ውስጥ ስንመለከት ጳውሎስ በጸሎት ሕይወቱ በግልጽ እናውቀዋለን:: ጳወሎስ ለራሱና ለሌሎች ይጸልይ ነበር:: ይህ ጸሎቱ የተጀመረው ወዲያው ከተለወጠ በኋላ ነው (ሐዋ 9:11):: ጳውሎስ በጸለየባቸው ክፍሎች ውስጥ ስንመለከት ብዙዎቹ ለሌሎች የጸለየባቸው የምልጃ ጸሎቶች ናቸው:: በአገልግታችን አማካይነት በሰዎች ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ዓላማ እንዲፈጸም ለምናገለግላቸው ሰዎች መጸለይ አለብን፡፡

*ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ <u>እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም::</u> በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ፥ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ <u>እንለምናለን</u>:: (ቆላስይስ 1፡9-12)*

### 9.7 <u>በጌታ በጽኑ በመታመን</u>

በክርስቶስ መታመን ለደህንነታችን ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ መንፈሳዊ ሕይወታችንም ወሳኝ እንደሆነ ጳውሎስ ያውቃል:: ይህ ብቻ ሳይሆን በአገልግሎታችን ውጤታማና ፍሬያማ መሆን እንድንችል ሁልጊዜ በእግዚአብሔር በፅኑ መታመን አለብን:: ከዚህ የተነሳ ስለለራሱና በአገልግሎቱ አጋሮቹ ስለሆኑት እንዲህ ብላል:-

*"እንግዲህ ሁልጊዜ <u>ታምነን</u> በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስም" (2 ቆሮ 5: 7)*

### 9.8 <u>መንፈሳዊ ስልጣናችንን በአግባቡ በመጠቀም</u>

መንፈሳዊ ስልጣን የምናገለግላቸውን ሰዎች ለማስፈራራትና እኛ ከእነርሱ እንደምንበልጥ የምናሳይበት ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠንን ጥሪና ተልዕኮ እንደ ባርያ ለመፈጸም ከሰማያዊው አምላክ የተላክን ለመሆኑ የምናሳይበት ልምምድ ነው፡፡

በሥልጣን እንድናገለግል የሚያደርገን መለኮታዊ ሥልጣን ያለው ቃል በእኛ መኖሩና በመንፈስ ቅዱስ ሃይል የሚሆን ለማግልገል የሚያስችለን ሰማያዊ ጸጋ ወይም ችሎታ እግዚአብሔር ስለሰጠን ነው:: ለዚህ ነው ጳውሎስ እንዲህ በማለት የተናገረው:-

***<u>አሕዛብ እንዲታዘዙ</u>** ክርስቶስ በቃልና በስራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ሐይል፣ በመንፈስ ቅዱስም ሐይል በእኔ አድርጎ ከሰራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም:: (ሮሜ 15: 19)*

*እምነታችሁ በእግዚአብሔር ሐይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን **<u>ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ሐይልን በመግለጥ ነበረ</u>** እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም:: (1 ቆሮ 2: 4- 5)*

ከዚህ እንደምናየው የጳውሎስ ሥልጣን ከራሱ ሳይሆን ከላይ ከእግዚአብሔር ነው።

## 10. አገልግሎትን የመፈጸም ውጤት ምንድን ነው?

### በአሁኑ ዘመን (በአሁኑ ዓለም)

#### 10.1 በእነርሱ ምክንያት እግዚአብሔር ይከበራል

*እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ (ዮሐንስ 17:4)*

#### 10.2 ለራሳቸው ትልቅ ማዕርግ ያገኛሉ (1 ጢሞ 3:13)

*በዲቁና ሥራ በመልካም ያገለገሉ ለራሳቸው ትልቅ ማዕርግና በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው እምነት ብዙ ድፍረት ያገኛሉ። (1 ጢሞቴዎስ 3:13)*

በክርስቲያኖች ዘንድ ክብርና ተቀባይነት ያገኛሉ። በትህትና፣ በታማኝነት፣ ራስን ዝቅ በማድረግ እና ክርስቶስን በሚመስል አገልግሎት ያገለገሉ ሰዎች በሌሎች ክርስቲያኖች ዘንድ ሞገስና ግርማ ስለሚኖራቸው የተከበሩ ናቸው። በአማኞች ፊት ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

#### 10.3 በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው እምነት ብዙ ድፍረት ያገኛሉ።

*በዲቁና ሥራ በመልካም ያገለገሉ ለራሳቸው ትልቅ ማዕርግና በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው እምነት ብዙ ድፍረት ያገኛሉ።* (1 ጢሞ 3:13)

በክርስቶስ ኢየሱስ ባላቸው እምነት ድፍረት፣ ዋስትናና እርግጠኝነት በውስጣቸው ይሰማቸዋል። ከክርስቶስ ጋር ያላቸው ሕብረትና አንድነት በእርግጠኝነት የተሞላ ይሆናል።

#### 10.4 ተጨማሪ በረከት፣ ጸጋ፣ ሃላፊነት፣ ደስታ ይቀበላሉ፤ በብዙ ይሾማሉ።

ጌታውም። መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፤ … (ማቴዎስ 5:21)

#### 10.5 በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጋሉ፣ መንፈሳዊ ፍሬ ያፈራሉ።

#### 10.6 ጸጋቸውን በመለማድ ያድጋሉ፣ ፍሬያማ አገልግሎት ማገልገል ይችላሉ።

### በሚመጣው ዓለም

#### 10.7 ወደ ጌታቸው ደስታ ይገባሉ

*ጌታውም፡- ። መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ … ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው። (ማቴዎስ 5:21)*

#### 10.8 አገልጋዮች ሽልማት ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ

በታማኝነትና በውጤታማነት አገልግሎታቸውን የፈጸሙ አገልጋዮች እግዚአብሔር ራሱ ሽልማት አዘጋጅቶላቸዋል።

*ወደ ፊት **የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥** ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም። (2 ጢሞቴዎስ 4፡8)*
*ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት **ደመወዙን ይቀበላል፤** (1 ቆሮንቶስ 3፡14)*
*ወንጌልን ብሰብክ እንኳ የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኛ ነውና፤ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ። ይህን በፈቃዴ ባደርገው **ደመወዝ አለኝና** ... (1 ቆሮንቶስ 3፡16-17)*
*እነሆ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል ክንዱም ስለ እርሱ ይገዛል እነሆ፥ **ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው።** (ኢሳይያስ 40፡10)*

### 10.9 እኛ በምድር ስናከብረው እርሱ በሚመጣው ዓለም ያከብረናል።

*እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ አሁንም፥ አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።*

ስለዚህ እግዚአብሔር እንደሰጠን ጥሪ፣ እንደተቀበልነውም አደራ አገልግሎታችንን እንፈጽም። አገልግታችንን ዓላማ ተኮር በመሆን እንድንፈጽም እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ጸጋውን ያብዛልን!